አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ
Addis Ababa City Government Revenues Bureau

ቀን
Date 5/8/15
ቁጥር
Ref. No. 10/1/9357/15

ለ ታክስ ጉዳዮች ዘርፍ
ለ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ አዲስ አበባ መካከለኛ ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት
ለ አዲስ አበባ መካከለኛ ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት
ለ መርካቶ ቁጥር 1 ቅ/ጽ/ቤት
ለ መርካቶ ቁጥር 2 ቅ/ጽ/ቤት
ለ አራዳ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ ቦሌ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ ቂርቆስ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ የካ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ አዲስ ከተማ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ ጉለሌ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ ኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ ልደታ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት
ለ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

<u>አ/አ/ገቢዎች ቢሮ</u>፣

የገቢ/ቀን 7/8/15.
የፓሮ/ቁጥር 34863.
የመሕ/ቁጥር

ጉዳዮ፡ - <u>የቤት ግብር ማሻሻያ ተግባራዊ እንዲደረግ ስለማሣወቅ</u>፤

የአዲስ አበባ ከተማ ፋይናንስ ቢሮ በቁጥር ፋ/ቢ/2/64/2249 በቀን 3/3/2015 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በከተማችን እያደገ የመጣውን የአገልግሎት ፍላጐት እና የመሠረተ ልማት አቅርቦት ችግሮችን ከመፍታት አንፃር ገቢን አሟጦ መሰብሰብ ማስፈለጉን ገልጾ የቦታ ኪራይና የቤት ግብር ግመታ ወቅታዊ ባለመደረጉ ከዚህ ዘርፍ የሚሰበሰበው ገቢ እጅግ አነስተኛ መሆኑና ችግሩን ለመፍታት ከባለድርሻ ተቋማት የተውጣጣ የንብረት ግብር ማስተግበሪያ ጊዜያዊ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በማቋቋም ወደ ሥራ መገባቱን አሣውቆናል፡፡

☎ የቢሮ ኃላፊ 0115575790 የጽ/ቤት ኃላፊ 0115575741 የሞ/ኮ/ስ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575748
የታ/ጉ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575608 የህግ ማ/ዘ/ም/ቢ/ኃላፊ 0115575604
Facebook page: Addis Ababa revenue bureau
Web site: http//aarevenue.gov.et
P.O.Box: 27400 Code 1000

የላቀ ገቢ ለአዲስ አበባችን ብልፅግና!

በመሆኑም ጊዜያዊ ፕ/ጽ/ቤቱ አሁን ያለውን ዓመታዊ የቤት ግብር ግምት ለማሻሻል የዳሰሣ ጥናት በማቅረብና በተገኘው የጥናቱ ውጤቶች ላይም ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አቅጣጫ የተሰጠበት በመሆኑ የገቢዎች ቢሮ የመሬት ተቋማት በሚልኩት የግብር ግምት መሠረት የቤት ግብሩ እንዲሰበስብ የተወሰነ በመሆኑ፣ በአድራሻ የተገለፀላችሁ ዘርፍና ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ወደ ተግባር እንድትገቡ የጥናት ውጤት ውሣኔውን እና አባሪ ደብዳቤውን 6 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር በማያያዝ የላክን መሆኑን እገልፃለሁ::

ከሰላምታ ጋር

አደም ኑሪ ዋበላ
የገቢዎች ቢሮ ኃላፊ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ * Addis Ababa City Government Revenue Bureau *

<u>ግልባጭ</u>፣

- ለ ሕግ ተገዥነት ሥራዎች ዘርፍ
- ለ ሞደርና/ኮር/ሥራዎች ዘርፍ
- ለ ቢሮ አማካሪ
- ለ ጽ/ቤት ኃላፊ

<u>አ/አ/ገቢዎች ቢሮ</u>፣

41815


በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
የፋይናንስ ቢሮ
ADDIS ABABA CITY GOVERNMET
FINANCE BUREAU


ቀን 3 /8/ 2015 ዓ. ም
Date

ቁጥር ፋ/ክ 12/64/2249
Ref No

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ለመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ

ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ

ለገቢዎች ቢሮ

<u>አዲስ አበባ</u>

<u>ጉዳዩ፡-የቤት ግብር ማሻሻያ ተግባራዊ እንዲደረግ ስለማሳወቅ ይመለከታል</u>

በከተማችን እያደገ የመጣውን የአገልግሎት ፍላጎት እና የመሰረተ ልማት አቅርቦት ችግሮችን ከመፍታት አንጻር ገቢን አሟጦ መሰብሰብ ያስፈልጋል።ስለዚህ በከተማ አስተዳደሩ ወሳኝ ከሆኑ የገቢ ዓይነቶች አንዱ የቤት ግብር (ንብረት ግብር) አንዱ ነው። ይሁን እንጂ በስራ ላይ ባለው የቦታ ኪራይና የቤት ግብር ግመታ ወቅታዊ ባለመደረጉ ምክንያት ከዚህ ዘርፍ የሚሰበሰበው ገቢ እጅግ አነስተኛ እንደሆነ መረጃዎች ያመላክታሉ።የህን ችግር ለመፍታት ከባለድርሻ ተቋማት የተውጣጣ የንብረት ግብር ማስተግበሪያ ጊዜያዊ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በማቋቋም ወደ ስራ ተገብቷል።

በዚሁ መሰረት ጊዜያዊ ፕ/ጽ/ቤቱ አሁን ያለው ዓመታዊ የቤት ግብር ግምት ለማሻሻል የዳሰሳ ጥናት በማድረግ ያቀረበ ሲሆን፣ በተገኙ የጥናቱ ውጤቶች ላይም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ማለትም የንብረት ግብር አስተግባሪ አብይ ኮሚቴ፣ የከተማ አስተዳደሩ የገቢ ግብረ ኃይል እንዲሁም ለፋይናንስ ቢሮ አመራሮች እና ለክፍለ ከተማ ጽ/ቤት ኃላፊዎች እና የስራ ሂደት አስተባባሪዎች በማቅረብ ውይይት የተደረገበት እና በተሰጠው ግብዓት መሰረትም ጥናቱ በአስቸኳይ ወደ ስራ እንዲገባ አቅጣጫ የተሰጠበት በመሆኑ የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ እና ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በጥናቱ መሰረት የንብረት ግብር ግምት ለገቢዎች ማሳወቅ እና እንዲሁም የገቢዎች ቢሮ የመሬት ተቋማት በሚልኩት የግብር ግምት መሰረት የቤት ግብሩ እንዲሰበሰብ እያሳወቅን በአሰራሩ ላይ ግልጽነት ለመፍጠር የቅርብ ክትትልና ድጋፍ የምናደርግ መሆኑን እያሳሰብን ፣ የጥናት ውጤት ውሳኔ --5-- ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ
የሪከርድ ስራ አመራር
Adiss Ababa City Government
Revenue Bureau Record Management

ከሰላምታ ጋር

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ፋይናንስ ቢሮ
Addis Ababa City Administration Bureau Of finance

አብዱልቃድር ሬድዋን ከማል
የፋይናንስ ቢሮ
ኃላፊ

<u>ግልባጭ</u> : -

- <u>ለክብርት ከንቲባ (እንዲያውቁት)</u>
- <u>ለከንቲባ ጽ/ቤት</u>
- በቢሮ ኃላፊ ደረጃ ለም/ቢሮ ኃላፊ (በጀት ዘርፍ)(ያለ አባሪ)
- በቢሮ ኃላፊ ደረጃ ለም/ቢሮ ኃላፊ (ፋይናንስ ዘርፍ)(ያለ አባሪ)
- ለንብረት ግብር አስተግባሪ ጊዜያዊ ፕ/ጽ/ቤት(ያለ አባሪ)

<u>ፋይናንስ ቢሮ</u>


011-155-26-80 Fax / ፋክስ 0111579810
205
E-mail: aa.cgfb@telecom.net.et

## የጥናት ውጤት ውሳኔ

የማዘጋጃቤታዊ ገቢን ለማሳደግ የተጻፉ ጹሁፎችና ጥናቶች እንደሚያስረዱት አንድ ከተማ አስተዳደር የሚሰጠውን አገልግሎቶች ለማስፋፋት እና እያደገ የመጣውን የነዋሪውን ፍላጎት ለማሟላት የገቢ ምንጮችን ማስፋትና የክፍያ ተመንን ወቅታዊ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ ነው። ስለሆነም በአጭርና በረዥም ጊዜ ውስጥ ማስተካከያ የሚፈልጉ ተመኖችን ለይቶ ጥናት በማድረግ ገቢን ማሳደግ እንደሚጠበቅ ያስቀምጣሉ።

የቤት ግብር አሁን በስራ ላይ ያለውን ህግ ማሻሻል ሳያስፈልግ ግብር ለመወሰን እና ለመሰብሰብ የሚያስችሉ ስልቶችን ተግባራዊ በማድረግ ከዘርፉ የሚሰበሰበውን ገቢ ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ የግብር ከፋዩን አቅም ያገናዘበ፣ የመሰረተ ልማት ጥያቄን የመለሰና የገንዘብ የመግዛት አቅምን ከግምት ውስጥ ያስገባ የግብር ማሻሻያ ውሳኔ እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. በከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር አዋጅ ቁጥር 80/1968 አንቀጽ 6/2 መሠረት የሚጣለውን የቤት ግብር መጠን በቤቱ ኪራይ ግምት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ይደነግጋል። እንዲሁም የቤት ኪራይ ግምት በዋናነት በቤቱ ዓይነት፣ ስፋትና አገልግሎት እና ቤቱ በሚገኝበት የቦታው ደረጃ መሠረት የሚለያይ መሆኑን በጥናት ማረጋገጥ ተችሏል። ስለሆነም በከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር አዋጅ ቁጥር 80/1968 አንቀጽ 6/2 ድንጋጌ መሠረት የቤት ኪራይ ግምት ለመገመት በጥናቱ የአንድ ሜትር ካሬ ወርሀዊ ኪራይ እንደሚከተለው ተለይቷል፡-

| የቦታ ደረጃ | ለመኖሪያ የሚያገለግል | | | ለመሥሪያ ቤት የሚያገለግል | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ከእንጨት እና ከጭቃ የተሰሩ ቤቶች | ኮንደሚኒየም | ቪላ (ከብሎኬት የተሰሩ) አፓርታማ እና ተመሳሳይ ህንጻዎች | ከእንጨት እና ከጭቃ የተሰሩ ቤቶች | ኮንደሚኒየም | ቪላ (ከብሎኬት የተሰሩ) አፓርታማ እና ተመሳሳይ ህንጻዎች |
| 1 | 214 | 247 | 361 | 444 | 493 | 632 |
| 2 | 156 | 182 | 317 | 417 | 428 | 542 |
| 3 ና 4 | 148 | 161 | 267 | 282 | 398 | 417 |

Adiss Ababa City Government
Revenue Bureau Record Management
የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
መዝገብ ቤት

2. የክፍያ ጫናውን ለማቅለል ሲባል የዚህ ዓመት ክፍያ ያልከፈሉ የቤት ግብር ከፋዮች በአንቀጽ 1 በጥናቱ በተለየው የአንድ ሜትር ካሬ የቤት ስፋት ወርሀዊ ኪራይ ግምት መጠንን ለመኖሪያ ቤት በ50% እና ለመሥሪያ ቤት ደግሞ በ75% ላይ ብቻ ግብሩ በማስላት እንዲከፍሉ ይደረጋል። ነገር ግን በቀጣይ በጀት ዓመት ለመኖሪያ ቤት እና ለመሥሪያ ቤት በሚያገለግሉ ቤቶች በአንቀጽ 1 የቤት ኪራይ ግምት መሠረት ግብሩ እየተሰላ የሚከፈልበት ይሆናል። በበዚህ ዓመት እንዲከፍሉ የሚጠበቁት የዚህ ዓመት ክፍያ ያልከፈሉት ብቻ ሆናል።

3. የቤት ግብር እንደሚከተለው ይሰላል፡-

የቤት ግብር = የቤቱ ስፋት x (ወርዊ ኪራይ x12) x የግብር መጣኔ

ለምሳሌ፡- በ1ኛ ደረጃ ቦታ የሚገኝ  እና 54 ሜትር ካሬ ስፋት ያለው ለመኖሪያ ቤት የሚያገለግል  ኮንዶሚኒየም ያለው ግብር ከፋይ የቤት ግብር እንደሚከተለው ይሰላል፡-
የቤት ግብር = 54x(247x12) x የግብር ምጣኔ = 7,097.52 ይሆናል።

➢ የከተማ ቤት ግብር ተመን ማስያ ሠንጠረዥ

| የዓመት የቤት ኪራይ ግምት በብር | ግብር የሚከፈልበት ገቢ መጠን | ምጣኔ | ግብር |
|---|---|---|---|
| እስከ 600.00 | 600.00 | 0.01 | 6.0 |
| 600.00-1,200.00 | 600.00 | 0.015 | 9.0 |
| 1,201.00-1,800.00 | 600.00 | 0.02 | 12.0 |
| 1,801.00- 2,400.00 | 600.00 | 0.025 | 15.0 |
| 2,401.00-3,600.00 | 1,200.00 | 0.03 | 36.0 |
| 3,601.00-4,800.00 | 1,200.00 | 0.035 | 42.0 |
| 4,801.00-6,000.00 | 1,200.00 | 0.04 | 48.0 |
| >6,000.00 | 154,127.28 | 0.045 | 6,935.72 |
| ድምር | | | 7,103.72 |

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ የሪከርድ ስራ አመራር
Adiss Ababa City Government Revenue Bureau Record Management

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መዝገብ ቤት

በዚህ ዓመት የሚወሰደው የግምቱን 50% በመሆኑ የቤት ኪራይ ግምቱ= ወደ 80,028 ዝቅ ይላል። በመሆኑም ግብሩ እንደሚከተለው ይሆናል

| የዓመት የቤት ኪራይ ግምት በብር | ግብር የሚከፈልበት ገቢ መጠን(ሀ) | ምጣኔ (ለ) | ግብር (ሀ*ለ) |
|---|---|---|---|
| እስከ 600.00 | 600.00 | 0.01 | 6.0 |
| 600.00-1,200.00 | 600.00 | 0.015 | 9.0 |
| 1,201.00-1,800.00 | 600.00 | 0.02 | 12.0 |
| 1,801.00- 2,400.00 | 600.00 | 0.025 | 15.0 |
| 2,401.00-3,600.00 | 1,200.00 | 0.03 | 36.0 |
| 3,601.00-4,800.00 | 1,200.00 | 0.035 | 42.0 |
| 4,801.00-6,000.00 | 1,200.00 | 0.04 | 48.0 |
| >6,000.00 | 74,028 | 0.045 | 3,601.26 |
| ድምር | | | 3,769.26 |

ስለሆነም በዚህ ዓመት የሚከፈለው የቤት ግብር = 3,769.26 ይሆናል ማለት ነው።

## 4. የባለድርሻ አካላት ተግባር እና ኃላፊነት በተመለከተ

የንብረት ግብር ስራ በባህሪው በአንድ ተቋም ብቻ ሊከናወን የሚችል ባለመሆኑ ባለድርሻ አካለት ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ የጥናት ቡድኑ በሰንጠረዡ ላይ የተዘረዘሩት በአጭር፣ በመካከለኛ እና በረጅም ጊዜ ወስደው ሊፈጽሟቸው የሚገባ ተግባራት እንደሚከተለው ቀርቧል።

| ተ.ቁ | ፈጻሚ ተቋማት | ተግባራት | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በአጭር | በመካከለኛ | በረጅም |
| | ከንቲባ ጽ/ቤት | • የተጠናው የንብረት (የቤት)ግብር ማሻሻያ ጥናት ወደ ተግባር እንዲገባ በየደረጃው ለሚገኘው አመራር የስራው ባለቤት እንዲሆን ማድረግ፣<br>• ከቢሮዎች አቅም በላይ የሆኑ ችግሮችን ተቋማትን በማስተባበር እንዲፈቱ ማድረግ፣ | • የተዘጋጀ የንብረት(የቤት) ግብር ረቂቅ አዋጅ በካቢኔ ታይቶ እና ማሻሻያ ተካቶበት ለከተማ አስተዳዳሩ ምክር ቤት እንዲጸድቅ መላክ፣ | |
| | ፋይናንስ | • ነባሩን ህግ መሰረት በማድረግ የንብረት ግብር ማሻሻያ ጥናት በማድረግ የውሳኔ | • ዘመናዊ የንብረት(የቤት) ግብር ስርዓትን ለመዘርጋት | • የንብረት (የቤት)ግብር |



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
መዝገብ ቤት
ፋይናንስ ቢሮ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ቢሮ | ኃሳብ ማቅረብ<br>• በነባሩ የቤት ግብርና የቦታ ኪራይ ህግ ላይ ተመስርቶ የተጠናውን የንብረት ግብር ማሻሻያ ሰነድ ወደ ትግባር ለማስገባት ለገቢዎች ቢሮ፣ለመሬት ልማትና አስተዳደርና ለመሬት ይዞታና መረጃ ኤጀንሲ አመራሮች እና ባለሙያዎች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን መስራት፣<br>• ረቂቅ የንብረት ግብር አዋጅ ማዘጋጀት፣ ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማቅረብና የመጨረሻ ረቂቅ ለከተማው ካቢኔ ማቅረብ፣ | የሚያስችሉ ጥናት ሰነዶችን ማዘጋጀት፣<br>• ዝርዝር የትግበራ የህግ ማዕቀፎችን ማዘጋጀት፣<br>• የንብረት ገበያ ጥናት እና ንብረቶች ዋጋ ግመታ ጥናት በአማካሪ ማስጠናት፣<br>• የዘመናዊ ንብረት ግመታና ግብር ስርዓት ለመዘርጋትና ለመተግበር በፌደራል ከተማና መሰረተ-ልማት በከተሞች ገቢ ሪፎርም ፕ/ጽ/ቤት የለማውን የንብረት ግብር ሶፍትዌር ወደ ስራ እንዲገባ ማድረግ፣ (የአቅም ግንባታ…) | ስርዓቱን በማዘመን ቋሚ አደረጃጀት እና ባለቤት እንዲኖረው ማድረግ<br>የሚያስችል ጥናት ማድረግ |
| 3 | ገቢዎች ቢሮ | • ማዘጋጃቤታዊ ታክስ ላይ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ማከናወን፣<br>• በህግ አተገባበር ላይ ያሉ ክፍተቶችን ማስተካከል (የወጪ ተቀናሽ ላይ)<br>• ከመሬት ልማትና አስተዳደር እና ከመሬት ይዞታና ምዝገባ ኤጀንሲ ተሰልቶ የቀረበለትን የንብረት ግብር መሰረት አድርጎ ማሳወቅና መሰብሰብ፣<br>• የግብር ከፋዮችን ዝርዝር መረጃ በመያዝ ተከታትሎ ማስከፈል፣ | • በፌደራል ደረጃ የለማውን የንብረት ግብር ሲስተም መጠቀም፣ | • የንብረት ግብር ስርዓቱን ማዘመን |
| 4 | መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ | • የይዞታ እና የማይንቀሳቀስ ንብረት በመመዝገብ ለመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ማስተላለፍ፤<br>• የመሬት እና መሬት ነክ መረጃዎችን የህንጻ ስፋት፣ የመሬት ስፋት እና የቦታ ደረጃ የሚገልጽ የይዞታ እና የቤት ፕላን በማደራጀት ለመሬት ይዞታና መረጃ ኤጀንሲ ማስተላለፍ፣<br>• የተሟላ መረጃ ያላቸውን ግብር ከፋዮች ማለትም የተረጋገጠ ይዞታ ያላቸውን፣ በቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የተመዘገቡትን የኮንደሚኒየም ቤቶች እንዲሁም በግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የተመዘገቡትን መረጃዎች | • ለንብረት(የቤት) ግብር አወሳሰን እና አስተዳደራዊ ቅለት የመሬት እና መሬት ነክ መረጃዎችን በዘመናዊ የመረጃ ስርዓት ማደራጀት እና ዳታ ቤዝ መመስረት፣<br>• በከተማ አስተዳደሩ የመሬት ልማት አስተዳደር ቢሮ የሚገኙ የመሬት ይዞታ ማህደር በውስጥ አቅም ማደራጀት እና ሲስተም ማልማት፣ወሳኝ መረጃ ስካን ማድረግ እና | • የመሬት ይዞታ ማህደር በዘመናዊ መልኩማደራጀት ለመሬትናመሬት ነክ ንብረት ምዝገባ ሂደት ለሚደረገው የይዞታ ማጣራት (Adjudication) እና ለንብረት ግብር ማዘመን ስራ ከፍተኛ ዕገዛ ስለሚያደርግ |

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሪከርድ ስራ አመራር
Addis Ababa City Government Revenue Bureau Record Management



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
መዝገብ ቤት
ፋይናንስ ጽ/ቤት

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | በመጠቀም በተቀመጠው ስሌት መሰረት የቦታ ኪራይ እና የንብረት(የቤት) ግብር በማስላት ለገቢዎች ማሳወቅ፣<br>• የቤት ሥሩት መረጃ የሌላቸው ግብር ከፋዮች ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን በተሰጣቸው የቤት ፕላን መሰረት የህንጻ ስፋት፣ እና የቦታውን ልዩ መጠሪያ እንዲያሳውቁ (self-declare) በማድረግ በቀረበው መረጃ መሰረት ለቦታ ደረጃው እና ለቤቱ ዓይነት በተወሰነው መሰረት ዓመታዊ የንብረት (የቤት)ግብር በማስላት ለገቢዎች ቢሮ ማሳወቅ፣ | ዳታ ቤዝ መመስረት ፣ | የመሬት ይዞታ ማህደር በካዳስተሩ ስታንዳርድ መሰረት ማደራጀት እና ዳታ ቤዝ ወይም ሲስተም ማልማት |
| 5 | የመሬት ይዞታና ምዝገባ ኤጀንሲ | • የተሟላ መረጃ ያላቸውን ግብር ከፋዮች ማለትም የተረጋገጠ ይዞታ ያላቸውን፣ በቤቶች ልማትና አስተዳደር ቢሮ የተመዘገቡትን የኮንደሚኒየም ቤቶች እንዲሁም በግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የተመዘገቡትን መረጃዎች በመጠቀም በተቀመጠው ስሌት መሰረት የቦታ ኪራይ እና የንብረት(የቤት) ግብር በማስላት ለገቢዎች ማሳወቅ፣<br>• የቤት ሥሩት መረጃ የሌላቸው ግብር ከፋዮች ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን በተሰጣቸው የቤት ፕላን መሰረት የህንጻ ስፋት፣ እና የቦታውን ልዩ መጠሪያ እንዲያሳውቁ (self-declare) በማድረግ በቀረበው መረጃ መሰረት ለቦታ ደረጃው እና ለቤቱ ዓይነት በተወሰነው መሰረት ዓመታዊ የንብረት(የቤት) ግብር በማስላት ለገቢዎች ቢሮ ማሳወቅ፣ | • በከተማ አስተዳደሩ የሚገኙ ንብረቶች መረጃ ለቀማና ዋጋ ግመታ በማካሄድ መረጃውን በመሰብሰብ ወደ ኮምፒውተር ማስገባት፣<br>• የመሬት ይዞታ ማህደር በካዳስተሩ ስታንዳርድ መሰረት እንዲደራጅ እና ዳታ ቤዝ ወይም ሲስተም ማልማት፣<br>• በፌደራል ደረጃ የለማውን የንብረት ግብር ሲስተም መጠቀም፣ | • የህጋዊ ካዳስተር ስራ በማጠናከር ለንብረት ግብር ወሳኝ የሆነውን የመሬት ነክ ንብረት መረጃ ለቀማ እና ግመታ ስራ ወይም ፊስካል ካዳስተር ተግባራዊ ቢደረግ፣ |

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ቢሮ
የሪከርድ ስራ አመራር
Adiss Ababa City Government
Revenue Bureau Record Management

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
መዝገብ ቤት
ፋይናንስ ቢሮ